# የቅዱሳት መጻሕፍት ጥናት

## አንደኛ ክፍል




በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
የመንበረ ፓትርያርክ (ዓለም አቀፍ) የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት

## መግቢያ

ልጆች በእግዚአብሔር ሰላምታ እንደምን አላችሁ! አባቶቻችን በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት በሚገባ ሠርተው ብራና ዳምጠው ፊደል ቀርጸው ጽፈው እንዲሁም በትውፊት (በቅብብሎሽ) መጻሕፍትን አዘጋጅተው ሰጥተውናል። እናንተም ቅዱሳት መጻሕፍትን በማወቅ እንድትተገብሩ በመልካም ሥነ ምግባር እንድትታነጹ ይህ መማሪያ መጽሐፍ ተዘጋጅቶአል: ስለዚህ በዚህ ክፍል ትምህርት ውስጥ የቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የቅዱሳን አባቶቻችን እና የቅዱሳን እናቶቻችን በሦስት ዋና ዋና ምዕራፎች ተካተው ቀርበዋል።

# መክስተ ርዕስ (ይዘት)

## አርእስት

መግቢያ
ምዕራፍ አንድ
ከአዳም እስከ ኖኅ ያሉ የአበው ታሪክ
፩. ፩ ሥነ ፍጥረት
፩. ፪ አዳም እና ሔዋን በኤደን ገነት
፩. ፫ የአቤልና የቃየን ታሪክ
፩. ፬ የኖኅ ታሪክ
፩ ፭ የባቢሎን ግንብ
ምዕራፍ ሁለት ........
ከአብርሃም እስከ ሙሴ
፪. ፩ የአባታችን የአብርሃም እና የሣራ ታሪክ
፪. ፪ የይስሐቅ ልደትና እድገት
፪. ፫ የያዕቆብ እና የኤሳው ታሪክ ......
፪. ፬ የያዕቆብ ልጆች ታሪክ..........
፪ ፭ የራሔል ታሪክ
፪. ፮ የያዕቆብ ልጅ የዮሴፍ ታሪክ
፪. ፯ የሙሴ መወለድና እድገት
፪. ፰ ለእስራኤላዊያን መና ከደመና መውረዱና ውኃ ከዓለት መፍለቁ
፪. ፱ የሙሴ እኅት ማርያም
ምዕራፍ ሦስት ...
ከኢያሱ እስከ ዳዊት..........
፫.፩. የኢያሱ ታሪክ
፫.፪. የሶምሶን ታሪክ
፫. የጌዴዎን ታሪክ
፫.፬. የሩት እና የኑኃሚን ታሪክ
፫፭ የሳሙኤል እናት የሐና ታሪክ

# ምዕራፍ አንድ
# ከአዳም እስከ ኖኅ ያሉ የአበው ታሪክ

## የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

- ሥነ-ፍጥረት ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡
- የሥነ-ፍጥረት አስገኚ ማን እንደሆነ ይገልጻሉ፡
- ከእሑድ ጀምሮ እስከ ቅዳሜ ድረስ የተፈጠሩ ፍጥረታትን ይዘረዝራሉ፡፡

## ቁልፍ ቃላት

- ሥነ ፍጥረት
- ፍጥረታት
- መሥዋዕት
- የኖኅ መርከብ
- የባቢሎን ግንብ

## የማስጀመሪያ ጥያቄዎች

፩. ልጆች ማን ፈጠራችሁ?
፪. የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ስም ማን ይባላል?
፫. ሥነፍጥረት ማለት ምን ማለት እንደሆነ እስኪ ለመምህራችሁ ተናገሩ።

## ፩. ፩ ሥነ-ፍጥረት

ሥነ-ፍጥረት ምንድን ነው?

ሥነ-ፍጥረት ማለት ከሁለት ቃላት የተገኘ ነው ። እነሱም "ሥነ" እና "ፍጥረት" ናቸው። ሥነ ማለት "ሠነየ" ከሚል የግእዝ ግስ የወጣ ሲሆን ያማረ፣ የተዋበ፣ የሚማርክ በሚል ቃል ይተረጐማል። ፍጥረት ማለት ደግሞ በእግዚአብሔር ስርዓት የተፈጠሩ ፍጥረታትን ያካትታል። ስለዚህ ሥነ-ፍጥረት ማለት ያማረ የተዋበ ደስ የሚል የእግዚአብሔር ፍጥረት ማለት ነው።

## የመልመጃ ጥያቄዎች

፩. ሥነፍጥረት ማለት ምን ማለት ነው?
፪. ልጆች ፍጥረታትን ያስገኘ ማን ነው?
፫. ልጆች ቀጣይ ገጽ ባለው ሥዕል ምን ምን ፍጥረታት ይታያችኋል።



ሥዕል ፩. ፩ ፡ ፍጥረታት

የፍጥረታት ቁጥራቸው እጅግ ብዙ ስለሆነ ተቆጥሮ የሚያልቅ ወይም ብዛታቸው ይህን ያህላል ተብሎ የሚገለጽ አይደለም፡፡ ነገር ግን ተመሳሳይ የሆኑትን ፍጥረታት አንድ ላይ እየመደብን ስንቆጥር አጠቃላይ የሥነ-ፍጥረት ብዛት ሃያ ሁለት (፳፪) ናቸው፡፡ እግዚአብሔር እነዚህን ሃያ ሁለት ፍጥረታት በስድስት ቀናት ፈጥሮአቸዋል፡፡ እነዚህም በስድስቱ ቀናት የተፈጠሩ ሃያ ሁለት ፍጥረታት የሚከተሉት ናቸው፡፡

የእሑድ /የመጀመሪያ ዕለት /ቀን/ ፍጥረታት ፰ ሲሆኑ እነርሱም ነፋስ፣ እሳት፣ መሬት፣ ውኃ፣ ጨለማ፣ ብርሃን፣ ሰማያት እና ቅዱሳን መላእክት ናቸው፡፡




ሥዕል ፩. ፪ የዕለተ እሑድ ፍጥረታት

የሰኞ ቀን ፍጥረት - ሰኞ ሁለተኛው ዕለት ሲሆን በዚህ ቀን አንድ ፍጥረት ተፈጥሯል:: እርሱም ጠፈር ነው::

የማክሰኞ ዕለት ፍጥረታት:- ማክሰኞ እግዚአብሔር ፍጥረታትን መፍጠር የጀመረበት ሦስተኛው ዕለት ሲሆን በዚህ ዕለት ዕፅዋት፣ አዝርዕት እና አትክልት ተፈጥረዋል::




ሥዕል ፩. ፫ የዕለተ ማክሰኞ ፍጥረታት

የረቡዕ ዕለት ፍጥረታት፡- እግዚአብሔር ፍጥረታትን መፍጠር የጀመረበት አራተኛው ዕለት ረቡዕ ሲሆን በዚሁ ዕለት ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት ተፈጥረዋል፡፡




ሥዕል ፩. ፬ ፡ የዕለተ ረቡዕ ፍጥረታት

የሐሙስ ዕለት ፍጥረታት፡- እግዚአብሔር በክንፍ የሚበሩ አእዋፍን፣ በእግር የሚሄዱ እንስሳትን፣ በደረታቸው የሚሳቡ ነፍሳትን፣ በየብስና በባሕር በሰማይና በምድር የሚኖሩ ፍጥረታትን ሁሉ በአምስተኛው ቀን ሐሙስ ዕለት ፈጥሯቸዋል: እነዚህ ፍጥረታት ከውሃ የተገኙ ናቸው።



ሥዕል ፩. ፫ የዕለተ ሐሙስ ፍጥረታት

እግዚአብሔር በስድስተኛው ዕለት በዕለተ ዓርብ በየብስ የሚኖሩ ፣ በሰማይ የሚበሩ አዕዋፋት ፣ አራዊት ፣ እንስሳት እና የከበረው ሰው አዳምን ፈጠረ: አዳም እና ሔዋንን (ሰዎች) አምላካቸውን በመልክ የሚመስሉ ብቸኛ ፍጡር ናቸው። እግዚአብሔር እነዚህን ሃያ ሁለት (፳፪) ፍጥረታት ከፈ ጠረ በኋላ በሰባተኛው ቀን ዐረፈ፡ ያም ቀን ሰንበት ተባለ።




ሥዕል ፩. ፲ የዕለተ ዓርብ ፍጥረታት

## የመልመጃ ጥያቄዎች

፩. ልጆች የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ ማን ነው?
፪. እግዚአብሔር በመጀመሪያ የፈጠረው ምንድን ነው?
፫. እግዚአብሔር በስንት ቀናት ፍጥረታትን ፈጠረ?
፬. እግዚአብሔር አዳምን መቼ ፈጠረ?

## ፩. ፪ አዳም እና ሔዋን በኤደን ገነት


### የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኂላ፦

- አዳም ሔዋንን “ሴት” ያለበትን ምክንያት ይገልጻሉ፤
- እግዚአብሔር ለአዳም ሔዋንን የፈጠረበት ምክንያትን ያብራራሉ፤
- የአዳምና የሔዋንን በኤደን ገነት የነበራቸውን ሕይወት እና የተባረሩበትን ምክንያት ያስረዳሉ።

### ሀ. የአዳምና የሔዋን አፈጣጠር

እግዚአብሔር አዳምን ከምድር አፈር በራሱ መልክ አስመስሎ ፈጠረው። ከሌሎች ፍጥረታት ለይቶ የሕይወትን እስትንፋስ ሞላበት ሕይወት ያለው ሠውም ሆነ። አዳም ማለት ያማረ የተዋበ ፍጥረት ማለት ነው። አዳም ሲፈጠር የሠላሳ አመት ሰው ነበር። እግዚአንሔርም አዳም ብቻውን መሆኑን አየቶ አዘነለት እግዚአብሔርም አዳም ከባድ እንቅልፍ እንዲወስደው አደረገና ከአዳም ጎን አንዷት አጥንት ወስዶ ስፍራውን በሥጋ ዘጋው። ከአዳም የወሰደውን አጥንት የዐሥራ አምስት ዓመት ሴት አድርጎ ፈጠራት።



ሥዕል ፩. ፯ ፡ አዳምና ሔዋን

አዳምም ባያት ጊዜ ደስተኛ ሆነ: የምታግዘው አብራው የምትሆን እና የምትመቸውን ረዳት በማግኘቱ "ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፣ ሥጋዋም ከሥጋዬ ናት እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል" አለ: አዳም ከረዳቱ ከሔዋን ጋር በአረንጓዴዋ ገነት አብሮ በደስታ መኖር ቻለ።

### የመልመጃ ጥያቄዎች

፩. አዳም ከተፈጠረ በኋላ ደስተኛ የሆነው ለምን ይመስላችኋል?
፪. አዳም ማለት ምን ማለት ነው?
፫. አዳም ሔዋንን ለምን ሴት ብሎ ጠራት?
፬. እግዚአብሔር ሔዋንን እንዴት አድርጎ ፈጠራት?

## ሊ. አዳምና ሔዋን በኤደን ገነት

ገነት ለማየት ደስ በሚያሰኙ፣ ለመብላት መልካም በሆኑ ዛፎች የተሞላች፣ በአራት ወንዞች የተከበበች ውብ ስፍራ ናት። ውብ በሆነችው ኤደን ገነት አዳም እና ሔዋን

ደስተኛ ሆነው መኖር ጀመሩ። አዳምም ከእግዚአብሔር ጋር ዕለት ዕለት ይነጋገር ነበር።


## የእግዚአብሔር ትእዛዝ

እግዚአብሔርም አዳምን “ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና” አለው። አንድ ቀን እግዚአብሔር እንስሳትን ሁሉ ወደ አዳም አመጣቸው፤ አዳምም ባያቸው ጊዜ ደስ አለው፡ ከእነርሱም ጋር መጫወት ጀመረ።

እግዚአብሔርም አዳምን ለእንሰሳቱ “ስም አውጣላቸው” አለው። አዳምም ሕያው ነፍስ ላላቸው ሁሉ ስም አወጣላቸው። አዳም ስለ  ሁሉም ነገር አምላኩን እግዚአብሔርን አመስገነ።


## አዳምና ሔዋንን ሰይጣን እንዳሳተቻው

ሰይጣን እግዚአብሔርን እና አዳምን ለማጣላት በእባብ ላይ አድሮ  ለሔዋን ክፉ ምክር አቀረበ ተንኮለኛው እባብ ሔዋንን “በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዟልን?›› አላት።  ሴቲቱም ለእባቡ “በገነት ካለው ከዛፉ ፍሬ እንበላለን፤ ነገር ግን ዕፀ በለስን እንዳንበላ እግዚአብሔር አዞናል” አለችው፡ ተንኮለኛው እባብም “ሞትን አትሞቱም ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ ይከፈታሉ እንደ እግዚአብሔርም መልካምና ክፉውን ታውቃላችሁ” አላት።



ሥዕል ፩.፰ ፡ አዳምና ሔዋን ዕፀ በለስን ሲበሉ

ፈታኙ እባብ ያቀረበውን ክፉ ምክር ሴቲቱ ሰማችው፤ ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደሆነ አየች። ከፍሬውም ወሰደችና በላች ለአዳምም ሰጠችው እርሱም ከእርሷ ጋር በላ። አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ሕግ አፈረሱ። እግዚአብሔርም ትእዛዙን ስላላከበሩ አዘነ። እግዚአብሔርም ወደ ገነት መጣ፡ አዳምም በገነት ጫካዎች ተደበቀ።



ሥዕል ፩. ፱ ፡ አዳምና ሔዋን ፈርተው ሲሸሽጉ

እግዚአብሔር "አዳም! አዳም! አዳም! ወዴት ነህ?" አለው። አዳምም "በገነት ድምፅህን ሰማሁ ራቁቴን ስለሆንሁ ፈራሁ ተሸሸግሁም" አለው። እግዚአብሔርም አዳምና ሔዋንን ቀጣቸው። ከውቧ ገነትም አባረራቸው፤ ገነትንም የሚጠብቅ የምትገለባበጥ የእሳት ሰይፍ የያዘ መልአክ አቆመ።



ሥዕል ፩. ፲ ፡ አዳምና ሔዋን ከገነት ሲወጡ

### የመልመጃ ጥያቄዎች

፩. አዳምና ሔዋን ከኤደን ገነት ለምን ተባረሩ?
፪. አዳምና ሔዋን እንዳትበሉ የተባሉት ምንድን ነው?
፫. እግዚአብሔርንና አዳምን ለማጣላት የፈለገው ማን ነው?


## ፩. ፫ የአቤልና የቃየን ታሪክ

### የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

- የአዳምና የሔዋንን የመጀመሪያ ልጆች ያውቃሉ
- የአቤልንና የቃየን የሥራ ድርሻ ይዘረዝራሉ፡፡
- የአቤልንና የቃየን መሥዋዕት ይገልጻሉ፡፡

አዳምና ሔዋን ከገነት ከተባረሩ በኋላ በዚህ ምድር ሲኖሩ ሔዋን ልጅ ወለደች: በዚህም ደስተኛ ስለነበረች “ወንድ ልጅ ከእግዚአብሔር አገኘሁ” ስትል ቃየን ብላ ስም አወጣችለት በመቀጠልም ሌላ ወንድ ልጅ ወለደች ስሙንም አቤል አለችው  አቤልና ቃየል ካደጉ በኋላ ቃየል ገበሬ ሆነ አቤል ደግሞ የበግ ጠባቂ ወይም አርቢ ሆነ፡፡



ሥዕል ፩. ፲፩ ፡ አቤል እና ቃየን

## የአቤል እና የቃየን መስዋዕት

ከዕለታት አንድ ቀን አቤልና ቃየል ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን ለማቅረብ አሰቡ። ቃየን ከምድር ፍሬ ወስዶ መሥዋዕት ሲያቀርብ “እግዚአብሔር አይበላው ምን ያደርግለታል” በማለት በግድ የለሽነት ከዘራው ሥንዴ ጥሩ ያልሆነ መሥዋዕትን አቀረበ አቤል ደግሞ “እግዚአብሔር በባሕርዩ ንጹሕ ስለሆነ ንጹሕ መሥዋዕት ይገባዋል” በማለት ከበጎቹ መካከል የተሻለውን በግ መርጦ መሥዋዕት ሰዋ።

ልጆች እግዚአብሔር የማንን መሥዋዕት የሚቀበል ይመስላችኋል? ልብን የሚመረምር አምላክ በንጽሕና እና በቅድስና የቀረበውን የአቤልን መሥዋዕት ተቀበለ። የቃየንን መሥዋዕት ግን አልተቀበለም።



ሥዕል ፩. ፲፪ ፡ አቤል እና ቃየን መሥዋዕት ሲያቀርቡ

## የቃየን በወንድሙ ላይ መቆጣት

ቃየንም እግዚአብሔር አቤልን እንጂ እርሱን እንዳልተቀበለው ባወቀ ጊዜ ተቆጣ በልቡ ክፉትን አሰበ: በመጨረሻም አቤልን “ወንድሜ ና ወደ ሜዳ እንሂድ” ብሎ ይዞት ሔደ:: በዚያም ቃየን ወንድሙን በድንጋይ ደብድቦ ገደለው: እግዚአብሔርም ቃየንን በክፉ ተቆጥቶ ቃየንንም ቀጣው: “ወንድምህ አቤልን ስለገደልከው የወንድምህ የደሙ ድምጽ ከምድር ወደ እኔ ይጮኻል:: በምድር ላይ የሚገድልህ አይኖርም ተቅበዝባዥ ትሆናለህ” ማንም እንዳይገድለው ምልክት አደረገበት::



ሥዕል ፩. ፲ : ቃየን አቤልን እንደገደለው

### የመልመጃ ጥያቄዎች

፩. የአዳምና ሔዋን የመጀመሪያ ልጆች ማን ማን ይባላሉ?

፪. አቤልና የቃየን ሥራቸው ምን ነበር?

፫. ከሁለቱ ወንድማማቾች ለአንተ/ለአንቺ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው ማን ነው? ለምን?

## ፩. ፬ የኖኅ ታሪክ

**የትምህርቱ ዓላማ**

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

- እግዚአብሔር በኖኅ ዘመን በኖሩ ሰዎች ለምን እንዳዘነ ይዘረዝራሉ፤
- ኖኅ መርከብን የሠራበትን ምክንያት ያብራራሉ፤
- ኖኅና ቤተሰቡ ከዘነበው ከጥፋት ውኃ እንዴት እንደዳኑ ይገልጻሉ።

የኖኅ አባት ላሜህ ይባላል፡ በእርሱ ዘመን ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ክፋዎች ዓመጽን ያበዙ፤ ሥነ ሥርዓት የማያከብሩ ቢሆንም እርሱ ግን አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገ መልካም ሰው ነበር እግዚአብሔር በኖኅ ዘመን ይኖሩ በነበሩ ሰዎች አዘነ፤ የንስሓም ጊዜ ሰጣቸው። ነገር ግን ሊመለሱ ፈቃደኞች ስላልሆኑ ቀጣቸው። ከዕለታት በአንድ ቀን እግዚአብሔር ኖኅን "ከእነርሱ የተነሣ ምድር በግፍ ተሞልታለችና እኔ አጠፋቸዋለሁ፡ አንተ ግን የምትድንበትን መርከብ ከጎፈር እንጨት ሥራ" አለው። ኖኅም እግዚአብሔር እንዳዘዘው መርከብን ሠራ።

ልጆች ኖኅ ለምን መርከብ እንዲሠራ ታዘዘ?

### የእግዚአብሔር ቁጣና ትእዛዝ

እግዚአብሔር ክፋዎችን የሚቀጣበት ጊዜ ደረሰ፡ ኖኅንም "አንተና ቤተሰቦችህን ሁሉ ይዘህ ወደ መርከብ ግባ አለው። ከሚበሉ እንስሳት ሁሉ ሰባት ሰባት ወንድ እና ሴት፡

ከማይበሉት እንስሳት ደግሞ ሁለት ሁለት ተባዕትና አንስት ከሰማይ አዕዋፋትም ወንድ እና ሴት እያደረግህ በምድር ላይ ለዘር ይቀሩ ዘንድ ለአንተ ትወስዳለህ" አለው።

ኖኅም ባለቤቱን ሴም ፣ ካም እና ያፌት የሚባሉ ልጆቹን ፣ የልጆቹን ሚስቶች እንዲሁም ከሁሉም እንስሳት ወንድና ሴት ይዞ ገባ፤ እግዚአብሔርም መርከቡን ከኋላ ዘጋበት። የሰማይ መስኮቶች ተከፈቱ የጥፋት ውኃ በምድር ላይ ያለማቋረጥ አርባ ቀንና ሌሊት ዘነበ። ምድር በሚያጠፋ ውኃ ተጥለቀለቀች። ክፉ ሰዎች ወደ ኖኅ መርከብ መግባት አልቻሉም። ቤቶቻቸው በጎርፍ ፈራረሱ። ምድር በውኃ ተሞላች፤ ተራሮች በውኃ ተሸፈኑ፣ ዓመፀኞቹም ሰጠሙ ማንም ሸሽቶ ማምለጥ አልቻለም የጥፋት ውኃው በቆመ ጊዜ የኖኅ መርከብ በአራራት ተራራ ዐረፈች። ኖኅም ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቀረበ፡ እግዚአብሔርም በሕያው ነፍስ መካከል ዳግመኛ በጥፋት ውኃ ምድርን ላያጠፋ ቃል ኪዳን አደረገ፤ የስምምነቱም ምልክት ቀስተ ደመና ነበር።



ሥዕል ፩. ፲፬ ፡ ጻድቁ ኖኅ

## የመልመጃ ጥያቄዎች

፩. እግዚአንሔር በኖኅ ዘመን የነበሩ ሰዎች ለምን ተቆጣ?
፪. የጥፋት ውኃው ሲቆም የኖኅ መርከብ ምን በሚባል ተራራ ላይ አረፈች?
፫. እግዚአብሔር ከኖኅ ጋር ላደረገው ቃል ኪዳን ምልክቱ ምንድን ነው?
፬. እግዚአብሔር ኖኅና ቤተሰቡን ለምን አዳነው?
፭. ከኖኅ ሕይወት ምን እንማራለን?
፮. የኖኅ ልጆች ስማቸው ማን ይባላል?

## ፩ ፭ የባቢሎን ግንብ

### የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

- የባቢሎን ሰዎች ምን እንደሠሩ ይዘርዝራሉ፤
- ባቢሎንን የሠሩት እነማን እንደሆኑ ይገልጻሉ፤
- የባቢሎን ሰዎች ቋንቋቸው ለምን እንደተደበላለቀ ያስረዳሉ።

## የባቢሎን ሰዎች

ሴም ካምና ያፌት የተባሉት የኖኅ ልጆች የልጅ ልጆችን ወለዱ በምድርም ላይ ሰዎች ከንፍር ውኃ በኋላ እየበዙ መጡ። የሚናገሩትም አንድ ቋንቋና አንድ ንግግር ነበረ። ከብዛታቸውም የተነሳ ከነበሩበት አገር ተነሥተው ሲጓዙ በሰናዖር አገር በጣም ሰፊ ሜዳ አገኙ ይህም ሜዳ በጣም ስለተስማማቸው በዚያ ለመኖር ወሰኑ። ከዚያም በእሳት ጡቦችን እየተኮሱ ትልልቅ ቤቶችንና ከተማን መሥራት ጀመሩ። በኋላም ስማቸውን ለማስጠራት ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ መሥራት ጀመሩ። በዚህ ሁሉ ነገር ላይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስላልጠየቁ ይልቁኑ የሚሠሩትን ክፉ ሥራ ሁሉ ስላወቀ ቋንቋቸውን ደበላለቀባቸው፡ በሰዎች መካከል አለመግባባት ስለተፈጠረ ግንቡን መሥራት ትተው ወደ የመንገዳቸው ሄዱ። የዚያችም የጀመሯት ከተማ ስም ባቢሎን ተባለ።



ሥዕል ፩. ፲፫ ፡ የባቢሎን ግንብ

## የመልመጃ ጥያቄዎች

፩. የባቢሎንን ግንብ የሠሩበት ሀገር ስም ማን ይባላል?
፪. የባቢሎን ሰዎች ቋንቋቸው የተዘበረዘረቀበት ምክንያት ምንድን ነው?
፫ ከባቢሎን ሰዎች ታሪክ ምን ትማራለህ/ ትማሪያለሽ?

## የማጠቃለያ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በትክክል ካነበባችሁ በኋላ ትክክል የሆነውን “እውነት” ትክክል ያልሆነውን ደግሞ “ሐሰት” በማለት መልሱ፡፡

፩. የመጀመሪያው ሰው ኖኅ ይባላል፡፡
፪ ቃየን አቤልን የገደለው እግዚአብሔር መሥዋቱን ስለተቀበለለት ቀንቶ ነው፡፡
፫. ሰው የተፈጠረው በዕለተ እሑድ ነው፡፡
፬. በኖኅ ዘመን የጥፋት ውኃ የዘነበው ሰዎች ጥሩ ስላደረጉ ነው፡፡
፭. በኖኅ ዘመን የነበሩ ሰዎች ሁሉም ቅዱሳን ነበሩ፡፡

ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ፡፡

፩. አዳም ማለት ምን ማለት ነው?
ሀ. የመጀመሪያ ፍጥረት
ለ. ያማረ ፍጥረት
ሐ. ሁሉን ቻይ

፪. ማክሰኞ ዕለት የተፈጠሩ ፍጥረታት ስንት ናቸው?
ሀ. አንድ
ለ. ሦስት
ሐ. ስምንት

፫. አዳም ከገነት የተባረረው ለምንድን ነው?

ሀ. ከሔዋን ጋር ተጣልቶ

ለ. የፈጣሪን ትእዛዝ አፍርሶ

ሐ. መሄድ ፈልጎ

፬. የኖኅ መርከብ ያረፈችበት ተራራ ምን ተብሎ ይጠራል?

ሀ. አራራት

ለ. ባቢሎን

ሐ. ኤልዳ

፭. ለኖኅ መርከብ እንዲያዘጋጅ የነገረው ማነው?

ሀ. አዳም

ሊ. እግዚአብሔር

ሐ. አቤል

በ "ሀ" ረድፍ ለሚገኙ ቃላትን በ "ለ" ረድፍ ከሚገኙ ስዕላት ጋር በመስመር አገኛኝ::


ሀ ለ

፩. እሁድ የተፈጠረው ፍጥረት

፪. ሰኞ የተፈጠረው ፍጥረት

፫. ማክሰኞ የተፈጠረው ፍጥረት

፬. ረቡዕ የተፈጠረው ፍጥረት



# ምዕራፍ ሁለት
# ከአብርሃም እስከ ሙሴ

## ፪.፩. የአባታችን የአብርሃም እና የሣራ ታሪክ

### የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦
- የአብርሃም እና የሣራ ታሪክን ያብራራሉ፤
- አብርሃም ከካራን ወደ ከንዓን የሄደበትን ምክንያት ይገልጻሉ፤

ዑር በተባለ ቦታ ይኖር የነበረ አብርሃም የተባለ አንድ ደግ ሰው ነበር። ከዕለታት በአንዱ ቀን እግዚአብሔር አብርሃምን “ከዘመዶችህ ተለይተህ ካራንን ለቀህ ውጣ እኔ ወደማሳይህ አገር ሂድ” ሲል አዘዘው። እርሱም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመስማት በዕድሜ የገፋው አብርሃምና ሚስቱ ሣራ እንዲሁም በርካታ አገልጋዮችና የአገልጋዮቹ ቤተሰቦች ከነአን ወደ ተባለው ቦታ ሲደርሱ እግዚአሔር አብርሃምን ጠርቶ የሰማይን ከዋክብት ተመልከት ሲል አዘዘው የምድርንም አሸዋ አሳየውና ዘሩን እንደ ሰማይ ከዋክብት እንደ ምድር አሸዋ እንደሚያበዛለት ቃል ገባለት አብርሃምም ወደ ከንዓን ገብቶ ኖረ። አብርሃምና ሣራ በከንዓን ሲኖሩ ሰው አክባሪና እንግዳ ተቀባዮች፣ ደጎችና እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች ነበሩ።

ሆኖም አብርሃምና ሣራ ልጅ አልነበራቸውም ዕድሜያቸውም ልጅ ለመውለድ አልፎባቸው ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን አብርሃም በቀትር በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ እንግዶች እየጠበቀ ሳለ እግዚአብሔር በሦስት ሰዎች አምሳል ተገለጠለት። ወደ ምድርም ሰገዶ ወደ ድንኳኑ እንዲገቡ ለመናቸው። ገብተው ከተስተናገዱ በኋላ ሚስቱ ሣራ ልጅ እንደምትወልድ ሲነግሩት አርጅተውና ልጅ የመውለጃቸው ጊዜ አልፎ ስለነበረ እንዴት ይሆናል ስትል ሣራ ሳቀች። ነገር ግን ሁሉን ቻይ የሆነው እግዚአብሔር አብርሃም መቶ አመት ሣራ

ደግሞ ዘጠና አመት ሆነው ሳሉ ልጅን ሰጣቸው ስሙንም ይስሐቅ አሉት።



ሥዕል ፪. ፩. እግዚአብሔር ለአብርሃም በሦስት ሰዎች አምሳል ሲገለጥለት

### የመልመጃ ጥያቄዎች

፩. አብርሃምና ሣራ ለምን ወደ ከንዓን ሄዱ?

፪. አብርሃም በመጀመሪያ ምን በተባለ ቦታ ይኖር ነበር?

፫. የአብርሃምና የሣራ ልጅ ማን ይባላል?

## ፬.፪ የይስሐቅ ልደትና እድገት

### የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

- የይስሐቅ ልደትና እድገት ያብራራሉ፤
- የይስሃቅ መልካም ባህርያትን ይዘረዝራሉ፤
- ይስሐቅ ለመሥዋዕት የቀረበበትን ምክንያት ይገልጻሉ፤
- በይስሐቅ ፋንታ (ምትክ) የተገኘው በግ ከየት እንደተገኘ ይናገራሉ።

ይስሐቅ በቅድስት ሥላሴ ብሥራት የተወለደ ልጅ ነው። እናትና አባቱ (አብርሃምና ሣራ) በእርጅና ዘመናቸው ነው የወለዱት። ይስሐቅ የተባለውም እግዚአብሔር ልጅ ትወልዳላችሁ ሲላቸው ሣራ የምወልድበት ጊዜ አልፏል ብላ ስቃ ስለነበር ነው።



ሥዕል ፬. ፪ ፡ ሣራ በኋላ ሆና ስትስቅ

## የይስሐቅ ታዛዥነት

ይስሐቅ እንደ ወላጆቹ እግዚአብሔርን የሚፈራ ቅን ትሑትና ታዛዥ ልጅ ነበር። አንድ ቀን እግዚአብሔር አብርሃምን "ልጅህን ይዘህ ወደ ሞሪያም ተራራ ውጣ በዚያም ለእኔ መሥዋዕት አድርገው።" አለው አብርሃምም እግዚአብሔርን ከመታዘዝ የሚያግደው ምንም ነገር አልነበረምና ልጁን ይስሐቅን ይዞ ሊሠዋው ወደ ተራራ ወጣ። በዚያም ለመሥዋዕት የሚያስፈልገውን እንጨት ሲያስተካክሉ ይስሐቅ "ለመሥዋዕት የሚያስፈልገውን ሁሉ አዘጋጀህ የሚሰዋው በግ ግን የት አለ?" ብሎ አብርሃምን ጠየቀ አብርሃምም "እግዚአብሔር ያዘጋጅልናል" ብሎ መለሰለት። በኋላ ላይ አብርሃም እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ ለይስሐቅ ከነገረው በኋላ በመሠዊያው እንጨት ላይ እንዲተኛ አዘዘው። ይስሐቅም ምንም ሳይከራከር የተባለውን አደረገ በተጨማሪ ለአባቱ እግሬንና እጄን እሰረኝ ሲል እራሱን እንደ በግ አቀረበ አባቱም ቢለዋውን አዘጋጅቶ ሊሰዋው ሲል እግዚአብሐር አብርሃምን እንዲህ አለው "አንድ ልጅህን ለእኔ አልከለከልክም በእኔ ላይ እምነት እንዳለህም ተመልክቻለሁና ተው አቁም በስተምሥራቅ በኩል ቀንዱ በዕፀ ሳቤቅ የተያዘውን በግ በልጅህ ፋንታ (ምትክ) ሠዋልኝ አለው አብርሃምም እንደተባለው አደረገ።



ሥዕል ፪. ፫ ፡ አብርሃም ልጁ ይስህቅን ሊሠዋው ሲል

### የመልመጃ ጥያቄዎች

፩. አብርሃም ይስሐቅን ሊሠዋ ይዞ የወጣበት ተራራ ማን ይባላል?
፪. በይስሐቅ ፋንታ የተሠዋውን በግ ከየማይ የሰጠው ማነው?
፫. አብርሃም እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘው ምን በማድረግ ነው?

## ፪.፫ የያዕቆብ እና የዔሳው ታሪክ

### የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

- የያዕቆብና የዔሳውን ታሪክ ይገልጻሉ፤
- የያዕቆብና የዔሳውን ተግባር ይገልጻሉ።።

የይስሐቅና የርብቃ መንታ ልጆች ዔሳውና ያዕቆብ ይባላሉ። ምንም እንኳን መንታ ቢሆኑም በመልክም ይሁን በፀባይ ምንም አይመሳሰሉም ነበር። ዔሳው እንስሳትን የሚያድን ሲሆን ያዕቆብ ደግሞ በቤት ውስጥ ሆኖ በጎችን የሚጠበቅ ልጅ ነበር።

ያዕቆብ በቤት ውስጥ እናቱን ርብቃን የሚያግዝና የሚታዘዝ እግዚአብሔርንም የሚፈራ ልጅ ነበር ከዕለታት አንድ ቀን ዔሳው ከአደን በጣም ደክሞት እና ርቦት መጣ። ወንድሙን ያዕቆብን በቤት ውስጥ የምስር ወጥ ሢሰራ አገኘው፡ ከሚሠራውም ምግብ እንዲሰጠው ጠየቀው። ምንም እንኳን መንታ ቢሆኑም የበለጠ በረከት የሚያገኘው የበኵር ልጅ ነው። በኵር ቀድሞ የተወለደ ማለት ነው። ዔሳው ይቀድመው ስለነበር ያዕቆብ በረከቱን ማጣቱ ይከነክነው ነበር። ስለዚህ “ምግብ እንድሰጥህ በኵርናህን ሽጥልኝ” ሲል ጠየቀው።

ዔሳው በጣም ርቦት ስለነበር እንዲሁም ለእግዚአብሔር በረከት ብዙም ግድ ስለሌለው ምንም ሳይከራከር "ውሰደው ከአሁን በኋላ አንተ ታላቅ ነህ ብቻ ምግቡን ስጠኝ" ሲል መለሰለት።



ሥዕል ፩. ፬ ፡ ያዕቆብና ዔሳው

## የይስሐቅ ምርቃት እና በረከት

ይስሐቅ የበኵር ልጁን የሚመርቅበት ጊዜ ደረሰና ዔሳውን እንዲህ አለው "አደን አድነህ ምግብ አዘጋጅልኝ ብሎ ላከው የያዕቆብ እና የዔሳው እናት ርብቃ የይስሐቅ ትእዛዝ ሰምታ ለሚታዘዛት ልጇ ያዕቆብ እንዲመረቅ ፊልጋ ከሚጠብቃጨው በጎች መካከል አባቱ የሚወደውን ዓይነት ምግብ አዘጋጀችና ያዕቆብ ዔሳውን መስሎ ገብቶ እንዲቀበል አደረገች። ይስሐቅም በእርጅና ምክንያት ዐይኑ ታውሮ ስለነበር ሊለየው አልቻለምና ለበኵር ልጅ የሚገባውን በረከት ለያዕቆብ ሰጠው።

በኋላም ዔሳው አደን አድኖ ምግብ አዘጋጅቶ ለአባቱ ይዞ ሲገባ ይስሐቅ ግራ ገባው የሆነውንም ሲነግረው ዔሳው በጣም ተናደደና ያዕቆብንም እንደሚገድለው ሲዝት እናቱ ሰማችው። ዔሳው ቂም ይዞ ወንድሙን እንዳይጐዳው አስባ ያዕቆብን ለማሸሽ ስትል ወደ ይስሐቅ ገብታ እንዲህ አለችው "ዔሳው እግዚአብሔርን ከማያመልኩ ከከነዓናዊያን መካከል ሚስት አግብቶ እግዚአብሔርንና እኛን እንዳሳዘነ አሁንም ያዕቆብ እንደ ወንድሙ ከከነዓን ሴቶች ከሚያገባ ወደ አባቴ ባቱኤል ቤት ይሂድና ሚስትን ለራሱ ያግባ።" ይስሐቅም በሐሳቧ ተስማምቶ ወደ ካራን ከተማ ላኩት።

### የመልመጃ ጥያቄዎች

፩. ከሁለቱ ወንድማማቾች እናቱን በሥራ ያግዝ የነበረው ማን ነበር?

፪. በኵር ማለት ምን ማለት ነው?

፫. ብኵርናን በምስር ወጥ የሸጠው ማነው? ለምን?

## ፪.፬ የያዕቆብ ልጆች ታሪክ

### የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

- የያዕቆብ እና የቤተሰቡን ታሪክ ይናገራሉ፤
- ያዕቆብ በስደት እያለ ምን እንደገጠመው ያብራራሉ።

ያዕቆብ ከወንድሙ ጋራ ከተጣላ በኋላ ወንድሙ ዔሳው እንዳይገድለው ፈርቶ ሸሽና ወደ አንድ ቦታ ደረሰ። ፀሐይ ጠልቃ ነበርና በዚያ አረፈ። በዚያ ስፍራ ደንጋይ ተንተርሶ ተኛ በሕልሙም ከምድር እስከ ሰማይ መሰላል ተዘርግቶ ተመለከተ የተኛበትንም ቦታ ቀደሰው ባረከው ያም ቦታ ቤቴል ተባለ።



*ሥዕል ፪. ፰ ፡ ያዕቆብ ሕልም ሲያልም*

ከዚያም ተነስቶ አጎቱ ላባ ዘንድ ወደ ካራን ሔደ: በዚያም ከአጎቱ ከላባ ጋር ኑሮ እስከ ሰባት አመት ድረስ ስለታናሺቱ ልጅ ስለ ራሔል የአጎቱን መንጋ በመጠበቅ አገለገለ፡ አጎቱ ላባም ራሔልን አቆይቶ በራሔል ፋንታ ልያን ተክቶ አጋባው፡፡ ያዕቆብም ለምን አታለልከኝ? ባለው ጊዜ የሰርጉ ቀኖች ከተፈጸሙ በኋላ ራሔልን ደግሞ እሰጥሀለሁና አንተም ሌላ ሰባት አመት ስለ እርሷ ታገለግለ ኛለህ በማለት ቃል ገባለት ያዕቆብም ራሔልን በጣም ይወዳት ስለ ነበር ተጨማሪ ሰባት ዓመት ካገለገለው በኋላ ያዕቆብ ራሔልን አጋብቶታል፡፡ ያዕቆብም በአጎቱ ሀገር ለሀያ ዓመታት ያህል ከኖረ በኋላ እግዚሔብሔር ወደ አባቱ ሀገር እንዲመለስ ነግሮታል፡፡ በሚመለስበት ወቅትም ጵኒኤል በምትባል ስፍራ እግዚአብሔር ተገል ጦለት ስምህ ያዕቆብ አይባል ከአሁን በኋላ ስምህ እሥራኤል ይባል ብሎ ስሙን ቀይሮለታል፡፡ ያዕቆብ በአጠቃላይ አስራ ሁለት (፲፪) ወንዶች ልጆች ሲኖሩት ከልያ፡- ሮቤል፣ ስምኦን፤ ይሁዳ፤ ይሳኮር እና ዛብሎን የተባሉ ልጆችን ወልዷል ከራሔል ደግሞ ዮሴ ፍንና ብንያ ምን ወልዷል፡፡ በተጨ ማ ሪም ከራሔልና ከልያ አገልጋዮች ዳንና ንፍታሌም ጋድና አሴር የተባሉ ልጆችን ወልዷል፡፡

**የመልመጃ ጥያቄዎች**

፩. ያዕቆብ አጎቱ ላባን ያገለገለው በአጠቃላይ ለስንት ዓመት ነው ?
፪. የራሔል ልጆች ስም ማን ነው?
፫ የያዕቆብ ስም እሥራኤል ተብሎ የተቀየረበት ቦታ የት ነው?

## ፪. ፭ የራሔል ታሪክ

ያዕቆብ /እሥራኤል/ በጣም ይወዳት የነበረችው ሚስቱ ራሔል ነበረች፡፡ ልያ የራሔል ታላቅ እኅት ለያዕቆብ ሮቤል፣ ስምኦን፣ ሌዊና ይሁዳን ወለደችለት፡፡ ራሔል ግን ልጅ አልነበራትም በዚህም በጣም ታዝንና እግዚአብሔርን አጥብቃ ትጠይቀው ነበር እንዲያ ውም አገልጋይዋን ባላን ለያዕቆብ ሚ ስት አድርጋ ሰጠችው ና ጋድንና አሴርን ወለደ፡፡ ልያ እንደገና ሁለት ወንዶች ልጆችን ማለትም ይሳኮርንና ዛብሎንን ወለደች፡፡ በመጨረሻም እግዚአብሔር የራሔልን ጸሎት ሰማና ዮሴፍን ወለደች፡፡ ራሔል ሁለተኛ ጸነሰች፡፡ ራሔል ሁለተኛ ልጇን ስትወልድ በምጥ ተይዛ ለመሞት በጣር ላይ እያለች ለልጇ ቤንኦኒ ብላ ስም አወጣችለትና ሞተች፡፡ አባቱም አስተክሎ ብንያም ብሎ ጠራው፡፡ በሚስቱም በራሔል ሞት እጅግ አዘነ፡፡

**የመልመጃ ጥያቄዎች**

፩. ራሔል ታዝን የነበረው በምን ክንያት ነው?
፪. ራሔል የወለደቻቸው ሁለቱ ልጆች ማን ማን ይባለሉ?

## የማጠቃለያ ጥያቄዎች

### የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በትክክል ካነበባችሁ በኋላ ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ፡፡

፩. አብርሃም ልጁ ይስሐቅን የወለደው በልጅነቱ ነው፡፡

፪. አብርሃም በእንግዳ ተቀባይነቱ ይታወቃል፡፡

፫. የእግዚአብሔርን ክብር ለፍጡራን መስጠት አምልኮ ባዕድ ይባላል፡፡

፬. ያዕቆብን እሥራኤል ብሎ የጠራው አባቱ ይስሐቅ ነው፡፡

፭. የወላጆች ምርቃት ለልጆች ጠቃሚ እንደሆነ የያዕቆብ ታሪክ ያሳየናል፡፡

### ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ፡፡

፩. ከካራን ወጥተህ ከንዓን ግባ የተባለው ማነው?

ሀ. አብርሃም

ሌ ይስሐቅ

ሐ. ያዕቆብ

፪. ብኵርናውን/የመጀመሪያ ልጅነቱን/ ለወንድሙ የሸጠው ማነው?

ሀ. ይስሐቅ

ለ. ያዕቆብ

ሐ ዔሳው

፫. እንደ ምድር አሸዋ አበዛዋለሁ ብሎ እግዚአብሔር ቃል የገባለት ማነው?

ሀ. አዳም

ሊ. አብርሃም

ሐ ኖኅ

፬. በቅድስት ሥላሴ መልካም ፈቃድ የተወለደ ልጅ ማን ይባላል?

ሀ. ይስሐቅ

ለ. ያዕቆብ

ሐ. ዔሳው

## ፪. ፯ የያዕቆብ ልጅ የዮሴፍ ታሪክ

### የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

- የዮሴፍን ታሪክን በቃል ይናገራሉ፤
- ዮሴፍ ወደ ግብጽ የተሸጠበትን ምክንያት ያስረዳሉ፤
- ዮሴፍ በግብጽ ሳለ እስር ቤት የገባበትን ምክንያት ይገልጻሉ።

ዮሴፍ ማለት "ይጨምር" ማለት ሲሆን የያዕቆብ አስራ አንደኛ ልጅ ለራሔል ደግሞ የመጀመሪያው ልጅ ነበረ። ከጠባዩ መልካምነት እና ከጥሩ ሥራው የተነሳ ከያዕቆብ ልጆች ሁሉ የተወደደ ሆነ ብዙ ሕልም ስላየ በተለይም ደግሞ እግዚአብሔር የገለጠለትን በወንድሞቹ ላይ አዛዥ የሚሆንበትን ሕልም አይቶ ለአባቱ ለያዕቆብ ሲነግረው ስለሰሙ ወንድሞቹ ጠሉት ሊገድሉትም ተማከሩ። በኋላ ግን ሐሳባቸውን ቀይረው ዮሴፍን ከግብጽ ለመጡ ነጋዴዎች ለባርነት ሸጡት።



ሥዕል ፪. ፯ ፡ ዮሴፍና ወንድሞቹ

ዮሴፍም በእግዚአብሔር ፈቃድ በግብጹ ፈርዖን ቤተ መንግስት የጥበቃዎች አለቃ በነበረው በጲጥፋራ ቤት ስለ ነበር በመልካም ጠባዩና በትሕትናው የፈርዖን ቤት አስተዳዳሪ ለመሆን በቃ:: ሆኖም የጲጥፋራ ሚስት ዮሴፍን በሐሰት ንጉሡ ፊት ስለከሰሰችው ወደ እስር ቤት ገባ::

## የመልመጃ ጥያቄዎች

፩. ወንድሞቹ ዮሴፍን ለምን ጠሉት?
፪. ዮሴፍ በግብፅ ሀገር ለምን ታሰረ?
፫. ዮሴፍ የፈርኦን ቤት አለቃ ለመሆን የበቃው በምን ምክንያት ነው?

## የዮሴፍ ቅንነት እና ታዛዥነት

ዮሴፍ በቀድሞው ጌታው ጲጥፋራ ቤት ባላጠፋው ጥፋት ምክንያት እስር ቤት ነበር:: ዮሴፍ በእስር ቤት ሰዎችን የሚረዳ እና ቅን ታዛዥ ነበር:: እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ስለነበር በእስር ቤት ውስጥ ኃላፊነት ሲሰጠው እስር ቤቱ ውስጥ ላሉ ሰዎች መልካም በማድረግ እና በመታዘዝ እስር ቤቱን የተሻለ ስፍራ አደረገው:: ዮሴፍ ቅን እና ታዛዥ ነበር::

## የዮሴፍ ሕልም የመፍታት ጸጋ

ዮሴፍ ሕልም የመፍታት ጸጋ ከእግዚአብሔር ተሰጥቶት ስለነበር በእስር ቤት ውስጥ ለነበሩ የንጉሡ ሁለት አገልጋዮች በሦስት ቀን ውስጥ ሕልማቸውን ፈታላቸው:: ከሁለቱ በእስር ቤት ከተጣሉ አገልጋዮች መካከል የአንዱን ከእስር ተፈትቶ ወደ ንጉሡ እንደሚ መለስ ገለጸለት ከእስር የተፈታው አገልጋይን ዮሴፍ እንዳይረሳው አሳስቦት ነበር ይህ አገልጋይ ግን ከእስር ከተፈታ በኋላ ዮሴፍን ለረጅም ጊዜ ረስቶት ነበር::

## የፈርዖን ሕልም እና የዮሴፍ ከእስር መፈታት

በኋላም ይህ አገልጋይ ፈርዖን ሕልም አይቶ ሕልሙን የሚፈታለት እንዳጣ በሰማ ጊዜ ዮሴፍን አስታውሶ የፈርዖንን ሕልም የሚፈታ ዮሴፍ የሚባል ወጣት ልጅ በእስር ቤት እንዳለ በመናገሩ ዮሴፍም የፈርዖንን ሕልም ለመፍታት ከእስር ቤት ወጥቷል:: ዮሴፍ

የፈርዖንን ሕልም በትክክል ስለፈታለትና ከጭንቀቱም ስለገላገለው በቤቱና በመንግሥቱ ላይ ሁሉ ባለሥልጣን አድርጎ ሾመው።



ሥዕል ፪. ፯ ንጉሡ ፈርዖን

## የመልመጃ ጥያቄዎች

፩. ዮሴፍ በእስር ቤት ሳለ የነበረው ሕይወት ምን ይመስል ነበር?
፪. ዮሴፍ በእስር ቤት ውስጥ ሳለ ለሁለቱ አገልጋዮች ምን አደረገ?
፫. ዮሴፍ በእስር ቤት ውስጥ መኖሩን ያስታወሰው ማን ነው?
፬. ዮሴፍ ተመልሶ በፈርዖን ቤት ሥልጣን ያገኘው በምን ምክንያት ነው?

## የዮሴፍ ዝና በፈርዖን ቤተ መንግሥት

ዮሴፍ ከእስር ቤት ከወጣ እና የፈርዖንን ሕልም ከፈታ በኋላ እንደ ሕልሙ ፍቺ ሰባት አመት እህል እየሰበሰበ በረኃብ ዘመን ብዙ ሰዎችን ለማትረፍ ቻለ:: የዮሴፍን ዝና የሰሙ ወንድሞቹ ወደግብጽ ሄዱ:: እሱም አባቱን ተቀብሎ የረኃቡ ዘመን እስኪፈፀም ድረስ ከእሱ ጋር እንዲቆዩ በማድረግ በወንድሞቹ ቂም ሳይዝ የረኃቡን ዘመን አሳለፋቸው:: ዮሴፍ አስናት የምትባል ግብፃዊት ሴት አግብቶ ኤፍሬምንና ምናሴን ወለደ ከዮሴፍ መልካም ሥራ የተነሣ አባቱ ብኵርናን (የመጀመሪያ ልጅ የሚያገኘውን ክብር) ለዮሴፍ በመስጠት ከክፉ ነገር ሁሉ ያዳነው የእግዚአብሔር መልአክ የዮሴፍን ልጆች እንዲባርክለት በጸሎት ጠየቀ:: እነርሱም በአባታቸው በዮሴፍ መልካም ሥራ በዝተው ነገደ ምናሴ እና ነገደ ኤፍሬም ተብለው ለመጠራት በቁ::



ሥዕል ፪. ፳ : የዮሴፍና ወንድሞች ለዮሴፍ ሲሰግዱ

ዮሴፍም እድሜው እየገፋ ሲመጣ “በምሞትበት ወቅት ግብጽ እንዳትቀብሩኝ ከዚህ አገር ወሥዳችሁ የአባቴ ሀገር ከነዓን እንድትቀብሩኝ” ብሎ ቃል በማስገባቱ በሞተ ጊዜ ወደ እስራኤል (ከንዓን) ወስደው ቀብረውታል::

### የመልመጃ ጥያቄዎች

፩. የዮሴፍ ልጆች ስማቸው ማን ይባላል?
፪. የዮሴፍ ወንድሞች ወደግብጽ ሃገር ለምን መጡ?

## ፪. ፯ የሙሴ መወለድና እድገት

### የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

- የሙሴን ታሪክ ይናገራሉ፤
- ከሙሴ ታሪክ ምን ትምህርት እንደምንማር ያስረዳሉ፤
- ሙሴ ሕዝቡን ከግብጽ ባርነት እንዴት እንዳዳናቸው ይገልጻሉ::

### የሙሴ ልደት እና የፈርዖን ቤተ መንግሥት

እስራኤላውያን በግብጽ ባርነት በነበሩበት ዘመን አንዲት እስራኤላዊት ሴት ወንድ ልጅ ወለደች: የወለደችው ወንድ ልጅ ከተገኘ የግብጹ ፈርዖን ስለሚገድልባት ደብቃ ለሦስት ወር ያህል አሳደገችው ከዚያ በላይ ግን መደበቅ ስላልቻለች ውኃ የማያስገባና የሚንሳፈፍ ሳጥን ሠርታ ልጇን ውስጡ አድርጋ እግዚአብሔርን ተማምና ወደ አባይ ወንዝ ለቀቀችው:: ከጥቂት ሰዓት በኋላም እንዳሰበችው የፈርዖን ልጅ ገላዋን ልትታጠብ ስትመጣ በውኃው ላይ የሚንሳፈፍ ቅርጫት መሳይ ነገር ተመለከተች:: አገልጋዮቿንም እንዲያመጡላት አድርጋ ስታስከፍተው በውስጡ ደስ የሚል ወንድ ልጅ አገኘች:: በጣም ደስ ብሏት ወሰደችው ከውኃው አውጥቼዋለሁና ስሙ ሙሴ ይሁን አለች:: ሙሴ ማለት

ከውኃ የወጣ ማለት ነው። ልጆች ሞግዚት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ? የሙሴ እኅት በሩቅ ሆና የሚሆነውን ትጠብቅ ነበርና ስትሮጥ መጥታ ለፈርዖን ልጅ ሞግዚት ላምጣልሽን? ስትል ጠይቃ ፈቃዷን አገኘች። ከዛም ፈጥና የሙሴን እናት ሕፃን ተንከባካቢ ሞግዚት ብላ አመጣችላት። የፈርዖን ልጅም "ልጁን አሳድጊልኝ የሚያስፈልገውን ሁሉ አሟላለሁ ደሞዝም እከፍልልሻለሁ" ብላት የራሷን ልጅ በእግዚአብሔር ጥበብ በነፃነት በቤተ መንግሥት የፈርዖን የልጅ ልጅ ሆኖ እንዲያድግ አደረገች። ሙሴን እንደ ሞግዚት ሆና ያሳደገችው እናቱ እስራኤላዊ እንደሆነ አባቶቹ እነማን እንደሆኑ እና ስለ አምላካቸው ስለ እግዚአብሔር ታስተምረው ነበር።



*ሥዕል ፪. ፱ የፈርዖን ልጅ ሙሴን ከባህር ላይ ስታገኘው*

በመጨረሻም የሁሉንም ግብጻውያን የበኩር (የመጀመሪያ ልጆች) በመቅሰፍት ሲመታቸው ፈርዖን ሕዝቡን ለቀቀ። ሕዝቡም ወደ ሀገራቸው በሚመለሱበት ወቅት እግዚአብሔር በተደጋጋሚ በሲና ተራራ ላይ ሙሴን ያነጋግረው ነበር፡ በተጨማሪም የቃል ኪዳኑን ታቦት ሰጥቶታል።

## የእስራኤል ወደ ከነአን መመለስ

እስራኤላውያን ወደ ከነአን እስኪደርሱ ድረስ እግዚአብሔር በታቦቱ ላይ እየተገለጸ ሙሴ እና ካህኑ አሮንን ያነጋግራቸው ነበር። ሙሴም ሕዝቡን ከምርኮ ነጻ ካወጣቸው በኋላ ለእነርሱ እግዚአብሔር ቃል የገባላቸውን ምድር ከንዓንን ሲወርሱ እርሱ ግን ምድረ ርስት ከንአንን ሳያይ በመንገድ ሳለ ሕይወቱ አልፏል።

### የመልመጃ ጥያቄዎች

፩. የቃል ኪዳኑን ታቦት የተቀበለው ማነው?

፪. ግብጽ በተለያዩ መቅሰፍቶች ለምን ተመታች?

፫. ሙሴ ይጠብቃቸው የነበሩ በጎች የማን ናቸው?

## ፪. ፰ ለእስራኤላዊያን መና ከደመና መውረዱና ውኃ ከዐለት መፍለቁ

### የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ለእስራኤላውያን በምድረ ባዳ የተደረገላቸውን ተዓምራት ያብራራሉ፤
- መና ከደመና መውረድ እና ውኃ ከዐለት መፍለቅ

ልጆች መና ማለት ምን ማለት ነው?

እስራኤላዊያን ከግብጽ ምድር ወጥተው በምድረ በዳ መጓዝ ከጀመሩ በኋላ በሙሴ ላይ "በቂ ምግብ ልናገኝ አልቻልንም በግብጽ ምድር ሞተን ቢሆን ይሻለን ነበር" ብለው አጉረመረሙ እግዚአብሔርም ከሰማይ ምግብ እንደሚሰጣቸው ነገራቸው በነጋታው በምድር ላይ ነጭ ነገር አዩና እርስ በርሳቸው "ይህ ምንድን ነው?" ተባባሉ እግዚአብሔር ከሰማይ የሰጣቸው ምግብ እንደሆነ ለቀኑ ብቻ የሚበቃቸውን መሰብሰብ እንዳለባቸው ሙሴ ነገራቸው:: እስራኤላዊያንም ያን ምግብ መና ብለው ጠሩት ጣዕሙም በማር እንደተሰራ ቂጣ ነበር:: እንደታዘዙትም ለቀኑ የሚበቃቸውን ብቻ ሰበሰቡ:: መና ቀን በቀን ከሰማይ ይወርድላቸው ነበር:: በስድስተኛው ቀን ግን እግዚአብሔር ለሁለት ቀን

የሚበቃቸ ውን ያህል እንዲሰበስቡ ነገራቸው:: በሰባተኛው ቀን የሰንበት ዕረፍት ነውና መና አያዘንብም እነሱም ለመልቀም አይወጡም ነበር:: እግዚአብሔር እስራኤላዊያንን በምድረ በዳ ጉዞአቸው ሁሉ ይህን መና የተባለውን ሰማያዊ ምግብ ያለማቋረጥ ይመግባቸው ነበር::



ሥዕል ፪. ፲ እስራኤላውያን መና ሲሰበስቡ

ልጆች ዐለት ማለት ምን ማለት ነው?

የሚጓዙበት መንገድ አብዛኛው በረሃ በመሆኑ ሕዝቡ በውኃ ጥም መቸገራቸውን የተመለከተው አምላክ ሙሴን በበትሩ ዐለቱን (ድንጊ ያውን) እንዲመታው አዘዘው በተባለው መሰረት ሙሴ ዐለቱን ሲ መታው ውኃ ፈልቆላቸዋል:: በእንደዚህ አይነት ተአምራት ከዐለት ላይ ውኃ እያፈለቀላቸው እነሱም የፈለቀውን ውኃ እየጠጡ ምድረ ርስትን ወርሰዋል::

### የመልመጃ ጥያቄዎች

፩. ለእስራኤላውያን ከሰማይ የወረደላቸው ምግብ ምን ይባላል?
፪. እግዚአብሔር ከዐለት ላይ ውኃ ባያፈልቅላቸው /ባያወጣላቸው/ ምን የሚሆኑ ይመስላችኋል?
፫. እስራኤላውያን መና የማይሰበስቡት በየትኛው ዕለት ነበር?
፬. ከሰማይ ሚወርደው ምግብ ጣዕም የምን ነበር?

## ፪. ፱ የሙሴ እኅት ማርያም ታሪክ

### የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

- የሙሴ እኅት ማርያምን ታሪክ ይናገራሉ።

የሙሴ እኅት ስሟ ማርያም ሲሆን ሙሴ በሕፃንነቱ እናቱ ወደ ባሕር በጣለችው ጊዜ በሩቅ ሆና የሚሆነውን ተከታትላ ለእናቷ የተናገረች ወንድሟን የምትወድ ልጅ ነበረች በኋላም የፈርዖን ሴት ልጅ ሙሴን ከተጣለበት ባሕር አውጥታ ስትወስደው እኅቱ ማርያም ወደ ፈርኦን ልጅ ዘንድ ሄዳ "ሕፃኑን ታጠባልሽ ዘንድ ሄጄ የምታጠባ ሴት ከዕብራዊያን ሴቶች ልጥራልሽን?" በማለት የሙሴን እናት በዘዴ ፈርዖን ቤት ገብታ ልጇን እንድታሳድግ ያደረገች ብልህ ሴት ናት። ሙሴ እስራኤልን እየመራ ባሕረ ኤርትራን ከፍሎ ከግብጽ ካወጣቸውና ጠላቶቻቸውንም በባሕሩ ካሰጠመላቸው በኋላ የሙሴ እኅት ማርያም በደስታ ከበሮዋን ይዛ እግዚአብሔርን በመዝሙር አመስግናለች።

## የመልመጃ ጥያቄዎች

፩. የሙሴ እኅት ስሟ ማን ይባላል?
፪. የሙሴ እኅት ወንድሟ ወደ ባሕር ሲጣልባት ምን አደረገች?
፫. ባሕረ ኤርትራን ከተሻገሩ በኋላ የሙሴ እኅት ማርያም ምን አደረገች?

## የማጠቃለያ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በትክክል ካነበባችሁ በኋላ ትክክል የሆነውን “እውነት” ትክክል ያልሆነውን ደግሞ “ሐሰት” በማለት መልሱ፡፡

፩. ዮሴፍ በሸጡት ወንድሞቹ ላይ ቂም ይዞ ነበር፡፡
፪ የዮሴፍ ታሪክ ይቅር ማለት እንዳለብን ያስተምራል፡፡
፫. የሙሴ ታሪክ ለሀገር ፍቅር ሊኖረን እንደሚገባ ያስተምራል፡፡
፬. ፈርዖን ሕዝ እስራኤልን ልቀቅ እንደተባለ ወዲያውኑ ቶሎ ለቀቃቸው፡፡
፭. እስራኤላውያን ውኃ ሳይጠማቸው ምድረ ርስት ገብተዋል፡፡

ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ፡፡

፩. ዮሴፍ በግብጽ ተወዳጅ ለመሆን የበቃው ለምን ነው?
ሀ. ትሑት ስለነበረ
ለ. ሐሰተኛ ስለነበረ
ሐ. ሀብታም ስለሆነ

፪. ዮሴፍ ወደ እስር ቤት የገባው በምን ምክንያት ነው?
ሀ. ዋሽቶ
ለ. በሐሰት ተከሶ
ሐ. ከሰው ተጣልቶ

፫. ዮሴፍ ከእስር ቤት ለመውጣት የቻለው በምን ምክንያት ነው?

ሀ. ሕልም በመፍታቱ

ለ. እስር ቤቱ በመሙላቱ

ሐ. በመታመሙ

፬. የሙሴ እናት ሙሴን ወደ ባሕር የጣለችው በምን ምክንያት ነው?

ሀ. ባለሥልጣን እንዲሆን

ለ. ንጉሡ እንዳይገድልባት

ሐ. ለፈርኦን ለመስጠት

፭. እግዚአብሔር ለሙሴ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገለጠበት ስፍራ ምን ይባላል?

ሀ. ቤተመቅደስ

ለ. ቤተመንግስት

ሐ. ሲና

፮. የቃል ኪዳኑን ታቦት ከእግዚአብሔር የተቀበለው ማነው?

ሀ. ዮሴፍ

ለ. አሮን

ሐ. ሙሴ

፯. ሙሴ ማለት ምን ማለት ነው?

ሀ. ከውኃ የተገኘ

ለ. ይጨምርልኝ

ሐ. አመስጋኝ

ባዶ ቦታዎቹን በተገቢው ቃል ሙሉ።

፩. በኵር ማለት ____________________ ማለት ነው።

፪. የሙሴ እኅት ስሟ ____________________ ይባላል።

፫. እስራኤላውያን ከሰማይ ይወርድላቸው የነበረው ምግብ ________________ ይባላል።

# ምዕራፍ ሦስት

## ከኢያሱ እስከ ዳዊት

### ፫.፩. የኢያሱ ታሪክ

#### የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦
- ኢያሱ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይገልጻሉ፤
- የኢያሱን ታሪክ ይናገራሉ፤
- ኢያሱ ያደረጋቸውን ሥራዎች ይገልጻሉ፤

#### ቁልፍ ቃላት

- ገባዖን
- ናዝራዊ
- መስፍን
- ስዕለት

ኢያሱ ማለት "እግዚአብሔር አዳኝ ነው" ማለት ሲሆን የአባቱ ስም ነዌ ይባላል፡፡ መንፈሳዊ አገልግሎት የጀመረው ሙሴ ከአማሌቃውያን ጋር እንዲዋጋ ባዘዘው ጊዜ ሲሆን ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የሙሴ የቅርብ ሰው ሆኖ ማገልገል ጀመረ፡፡ ሙሴ ከሞተ በኋላ እግዚአብሔር ኢያሱን ሕዝቡን እንዲመራ እና ለአባቶቻቸው የገባውን ቃል ኪዳን ከነዓንን እንዲያወርስ መረጠው፡፡ የእስራኤል ሕዝብ በኢያሱ መሪነት ዮርዳኖስን ተሻግረው ኢያሪኮን ያዙ፡፡ እግዚአብሔር ቀኑን በማርዘም እና በገባዖን ሰማይ ላይ ፀሐይን በማቆም እና በረዶ በማዝነብ ረዳቸው፡፡

በመጨረሻም በእግዚአብሔር ኃይል እና በኢያሱ መሪነት እስራኤል ከነዓንን ወረሱ፡፡ ኢያሱ መሬቱን ለእስራኤል ነገዶች አከፋፈለ፡፡ ከዚህ በኋላ ኢያሱ የመሞቱ ጊዜ ሲቀርብ ሕዝቡን ሰብስቦ እግዚአብሔር ከአባቶቻቸው ከነ አብርሃም ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ያደረገላቸውን ውለታ እንዳይረሱ አስጠነቀቃቸው፡፡ ኢያሱ በዘመኑ ሁሉ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ብቻ እንዲያመልኩና እንዲያገለግሉ አደረገ፡፡ ኢያሱ በመቶ ዐሥር ዓመቱ ሞተ፡፡ ሕዝቡም በርስቱ በኤፍሬም አገር ቀበሩት፡፡

## የመልመጃ ጥያቄዎች

፩. ኢያሱ ማለት ምን ማለት ነው?
፪. ኢያሱ እግዚአብሔርን እንዲያገለግል የመረጠው ማነው?
፫. ኢያሱ የሚሞትበት ጊዜ ሲደረስ ሕዝቡን ሰብስቦ ምን አደረገ?
፬. በኢያሱ መሪነት ሕዝቡ የተሻገሩት ወንዝ ምን ይባላል?

## ፫.፪ የሶምሶን ታሪክ

### 👑 የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

- የሶምሶንን ታሪክ ይናገራሉ፤
- ሶምሶን የሠራቸውን ሥራዎች ይዘረዝራሉ፤
- የሶምሶን ኃይሉ ምን እነደሆነ ይለያሉ፡፡

### የሶምሶን ታሪክ የተሰጠው ኃይል

ሶምሶን የሚባል አንድ ወጣት ነበር፡፡ አባቱ የዳን ነገድ የሆነ ማኑሄ የሚባል ሰው ነበር፡፡ እናቱ መካን ነበረች፡፡ የእግዚአብሔር መልአክ ልጅ እንደምትወልድ ነገራት፡፡ ሶምሶን ከልደቱ ጀምሮ ናዝራዊ ስለነበረ ፀጉሩን አይላጭም ነበር፡፡ የሚያሰክር መጠጥም አይጠጣም ነበር፡፡ የእግዚአብሔርም ኃይል በፀጉሩ ላይ ነበረ፡፡



ሥዕል ፫. ፩ ፡ ሶምሶን አንበሳን ሲገድል

ልጆች አንበሳ አይታችሁ ታውቃላችሁ ?

በአንድ ወቅት ሶምሶን ከእናቱና ከአባቱ ጋር ወደ ተምና ከተማ ሄደ:: በዚያም አንድ የአንበሳ ደቦል እያገሳ ወደ እርሱ መጣበት፡ ሶምሶንም ያለ መሣሪያ በእግዚአብሔር ኃይል አንበሳውን ገደለው:: ከጥቂት ቀን በኋላ የአንበሳውን ሬሳ ሊያይ ተመለሰ::

ሶምሶንና ፍልስጥኤማውያን

ሶምሶን ፍልስጥኤምን እንዲወጋ ኃይል ከእግዚአብሔር ተቀበለ:: አንዲት ፍልስጥኤማዊት ሚስት አገባ:: በእርሷም ምክንያት በተጣሉ ጊዜ እህላቸውን አቃጠለ:: በአንድ የአህያ መንጋጋ አንድ ሺህ ፍልስጥኤማውያንን ገደለ::

በአንድ ወቅት ጠላቶቹ በጋዛ ከተማ ሊይዙት ሲጠባበቁት የከተማይቱን በር መዝጊያ ነቅሎ በመውሰድ አመለጠ:: ሶምሶን ደሊላ የምትባል ሴት ወደደ:: ይህች ሴት ኃይሉ ያለበትን የአካል ክፍል፤ የናዝራዊነቱን ምሥጢር እስኪነግራት ድረስ በፍቅር አታለለችው:: ኃይሉ በፀጉሩ እንደሆነ ሲነግራት ፀጉሩን ላጭታ ሲደክም ለፍልስማጥኤውያን መኳንንት አሳልፋ ሰጠችው::

ሶምሶን ኃይለኛ የሆነው በእምነት ነበር፡ ራሱን ባለመግዛቱ ምክንያት ኃይሉን አጣ:: ጠላቶቹ በእስር ቤት ጣሉት:: ዓይኖቹን አውጥተው አሳወሩት:: በመጨረሻም ወደ እግዚአብሔር ጸልዮ የቤቱን ምሰሶዎች ገፋው ቤቱ ሲወድቅ በቤቱ የነበሩት ሰዎች በሙሉ ሞቱ::

## የመልመጃ ጥያቄዎች

፩. ናዝራዊ ማለት ምን ማለት ነው?
፪. ሶምሶን መሳርያ ሳይጠቀም የገደለው እንስሳ ምንድነው?
፫. ሶምሶን ለምን ኃይሉን አጣ?
፬. ሶምሶንን ያታለለችው ሴት ማን ናት?
፭. የሶምሶን ኃይል ምኑ ላይ ነበር?

## ፫.፫ የጌዴዎን ታሪክ

ጌዴዎን በእስራኤል ከሚታወቁ መሳፍንት መካከል አንዱ ነው። በዋሻ ውስጥ ሆኖ ስንዴ ሲወቃ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከአማሌቃው ያን እንዲያድን ጠራው፡ ጌድዮንም ከሕዝቡ ውስጥ ሦስት መቶ ወታደሮችን ብቻ ይዞ አማሌቃውያንን አሸነፋቸው። ሕዝቡም በድሉ ተደስተው ንጉሥ ሁንልን ብለው ቢጠይቁት ጥያቄያቸውን ሳይቀበል በመስፍንነት ብቻ እስራኤልን ሲያገለግል ኖረ።

### የመልመጃ ጥያቄዎች

፩. መስፍንነት ማለት ምን ማለት ነው?
፪. ጌድዮን ያሸነፋቸው ሰዎች የየት ሀገር ሰዎች ነበሩ?

### የማጠቃለያ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በትክክል ካነበባችሁ በኋላ ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

፩. ኢያሱ ለአገልግሎት የተጠራው በሙሴ አማካይነት ነው ፡፡

፪. ሶምሶን ማለት እግዚአብሔር አዳኝ ነው ማለት ነው።

፫. ጌዴዎን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለነበር በሦስት መቶ ወታደሮች ብቻ ጠላቶቹን አሸነፈ።

፬. ሶምሶን ናዝራዊ ይሆናል የተባለው በስዕለት ስለተወለደ ነው።

፭. ሶምሶን ጠንካራ ወጣት ነበር፡ የእግዚአብሔርም ኃይል በእርሱ ነበር።

ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ።

፩. በገባዖን ፀሐይን ያቆመው ማነው?

ሀ. ሙሴ

ለ. ኢያሱ

ሐ. ሶምሶን

፪. ሶምሶን ኃይሉን ያጣው በምን ምክንያት ነው?

ሀ. ምሥጢሩን በመናገሩ

ለ. ጸሎት በማድረጉ

ሐ. ናዝራዊ መሆኑን ስላወቀ

፫. የእግዚአብሔር ኃይል በሶምሶን በየትኛው የአካል ክፍሉ ነበር?

ሀ. በእግሩ

ለ. በፀጉሩ

ሐ. በእጁ

## ፫.፬ የሩት እና የኑኃሚን ታሪክ

### የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

- የኑኃሚንን ታሪክ ይናገራሉ፤
- ሩት ያደረገችውን መልካም ነገር ይገልጻሉ።

ኑኃሚን ማለት ደስታዬ ማለት ነው። በእስራኤል የሚኖር አቤሜሌክ የሚባል ካህን ነበር። በሀገሩ ድርቅ ቢበረታባቸውና ሰው ሁሉ ወደ ሌላ ሀገር ሲሰደድ አቤሜሌክም ሁለት ወንዶች ልጆችንና ኑኃሚንን ይዞ ሞአብ ወደ ምትባል አገር ተሰደደ። በዚያም እያሉ ሁለቱ ልጆቹ ከሞአብ ሴቶች መሐል ዖርፋ እና ሩት የሚባሉ ሴቶችን አገቡ። መጀመሪያ ካህኑ አቤሜሌክ በመቀጠልም ሁለቱ ወንዶች ልጆቿ ሞቱባት። ተስፋ ቆርጣ ወደ ሀገሯ ስትመለስ ሩት አብሬሽ ወደ አንቺ ሀገር እሄዳለሁ እንጂ ሌላው ሁሉ ሲተውሽ እኔ አልተውሽም ብላ ተከትላ ወደ እስራኤል መጣች። ትንሽ ቆይታ ቦኤዝ የሚባል የኑኃሚንን ዘመድ አግብታ ኢዮቤድ የሚባል ልጅ ወለደች። እርሱም የንጉስ ዳዊት አያት ለመሆን በቃ።



ሥዕል ፫. ፪፡ ሩት የቦኤዝን እርሻ ስትቃርም

**የመልመጃ ጥያቄዎች**

፩. ኑኃሚን ማለት ምን ማለት ነው?


፪ ኑኃሚን በጣም ተስፋ ቆርጣ ወደ ሀገሯ የተመለሰችው ለምንድን ነው?

፫. የዳዊት አያት የተባለው ማን ነው?

## ፫.፭ የሳሙኤል እናት የሐና ታሪክ

በተራራማው በኤፍሬም ሀገር የሚኖር ሕልቃና የሚባል አንድ ሰው ነበር። ሕልቃና ሐና የምትባል ሚስት ነበረችው። ሚስቱ ሐና መካን ስለነበረች ልጅ አልነበራትም። በዚህ የተነሳ ብዙ ጊዜ ሐና ታለቅስና ታማርር ነበር፡ ምግብም አትቀምስም ነበር። ባሏ ሕልቃና ሊያጽናናት እንኳን ቢሞክር ሐና በጣም አዝና ስለነበር ወደ ቤተመቅደሱ ብቻዋን ሔዳ እግዚአብሔር ልጅ እንዲሰጣት ትለምን ነበር። እርሱ የሚሰጣትን ልጅ መልሳ ለእግዚአብሔር እንደ ምትሰጥ ስ ዕለት ተሳለች። እያለቀሰች ጸሎቷን ወደ እግዚአብሔር አቀረበች። ሐና ስትጸልይ ካህኑ ዔሊ በቤተመቅደስ ደጃፍ ተቀምጦ ይመለከት ነበር። ሐና

የወይን ጠጅ ጠጥታ ስክራ የምትለፈልፍ መሰለው:: "የወይን ጠጅሽን ከአንቺ አርቂው" ሲል ሐናን ተናገራት: ሐና ግን የወይን ጠጅ ጠታ የምትለፈልፍ ሴት አልነበረችም:: እግዚአብሔር ልጅ እንዲሰጣት በጸሎት እየጠየቀች እንደሆነ ለእግዚአ ብሔር ካህን አስረዳችው:: የእግዚአብሔር ካህን ዔሊ "የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር የለመንሽውን ልመና ይስጥሽ" ብሎ ባረካት:: ሐናም ደስተኛ ሆና ወደ ቤቷ ተመለሰች እግዚአብሔርም የሐናን ልቅሶና ልመና ሰማ:: የመውለጃዋ ወራት ሲደርስ ሐና ወንድ ልጅ ወለደች:: እግዚአብሔር ልመናዬን ሰምቷል ስትል ስሙን ሳሙኤል ብላ ጠራችው::



ሥዕል ፫. ፫ ፡ የሳሙኤል እናት የሐና

## የሕፃኑ ሳሙኤል ለቤተክርስቲያን መሰጠት

ሐናም ሕፃኑ ሳሙኤልን ጡት እያጠባች ጡት እስኪተው ድረስ በቤትዋ ተቀመጠ:: ሕፃኑ ሳሙኤል ጡት መጥባት በተወ ጊዜ ሳሙኤልን እና ለመሥዋዕት የሚሆኑ ነገሮችን ይዛ ወደ እግዚአብሔር ቤት መጣች:: ሕፃኑ ሳሙኤልን በእግዚአብሔር ካህን በዔሊ ፊት ይዛ ሄደች:: እግዚአብሔር የለመንሁትን ልመናዬን ሰጥቶኛል እኔም ደግሞ ለእግዚአብሔር ሰጥቼዋለሁ ዕድሜውን ሁሉ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ይሆናል" ብላ ሳሙኤልን ለካህኑ ዔሊ ሰጠችው:: እግዚአብሔር ልመናዋን ስለተቀበለ ሐና ፈጣሪዋን አመሰገነች:: ሳሙኤል ከዚያን ቀን ጀምሮ ከካህኑ ዔሊ ጋር በቤተመቅደስ መኖር ጀመረ: ካህኑ ዔሊ ሳሙኤልን የእግዚአብሔርን ቃል እያስተማረ በቤተ መቅደስ ያሳድገው ይንከባከበውም ነበር::



ሥዕል ፫.፬ ሕፃኑ ሳሙኤል ለቤተክርስቲያን መስጠት

## የመልመጃ ጥያቄዎች

፩. ሐና ታዝን የነበረው ለምንድነው?

፪. ሳሙኤል ማለት ምን ማለት ነው?

፫. ሐና በቤተመቅደስ ያገኘችው ካህን ማን ነበር?

፬. ዔሊ ሳሙኤልን እያስተማረ ይንከባከበው የነበረው ለምንድነው?

## የማጠቃለያ ጥያቄዎች

### ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ።

፩. ሰው ቢተውሽ እኔ ግን አልተውሽም ብላ ኑኃሚንን ተከትላ ወደ እስራኤል የመጣች ሴት ማን ናት?

ሀ. ሩት

ለ. ዖርፋ

ሐ. የሳሙኤል እናት ሃና

፪. ልመናዋን ሰምቶ ልጅ ስለ ሰጣት እግዚአብሔርን በጸሎት ያመሰገነች ሴት የትኛዋ ናት?

ሀ. ኑኃሚን

ለ. የሳሙኤል እናት ሐና

ሐ. የኢዮቤድ እናት ሩት